# ልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ብዝበዛ እና የሥራ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ

አዲስ አበባ ዉስጥ በልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ስርጭት ላይ የተሰራ መጠነ-ሰፊ ጥናት ዋና ዋና ግኝቶች

የቤት ውስጥ ሥራ እንደ 'የግል አገልግሎት' ስለሚቆጠር አሁን ባለው የኢትዮጵያ የሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ሽፋን አልተሰጠዉም

**37%** ይህ ጥናት የተደረገበት አከባቢ 37 በመቶ የሚሆኑ ልጃገረዶች የቤት ዉስጥ ስራ ላይ ተሰማርቷል

## በአዋጁ የተደነገጉ፡

ወጣት ሰራተኞች (ከ15-17 አመት) በሳምንት ከ42 ሰዓት በላይ እንዳይሰሩ ይደነግጋል።

ወጣት ሠራተኞች ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት በፊት ወይም ከቀኑ 10፡00 ሰዓት በኋላ እንዳይሰሩ ይደነግጋል።

ወጣት ሠራተኞች ቢያንስ በሳምንት አንድ የእረፍት ቀን እንዲኖራቸዉ ይደነግጋል።

ወጣት ሠራተኞች ህዝባዊ በዓላት ላይ እንዳይሰሩ ይደነግጋል።

## ልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች የስራ ሁኔታ፡

በአማካይ በሳምንት ዉስጥ **55** ሰዓታት ይሰራሉ፤

**31%** ከጥዋቱ12፡00 ሰዓት በፊት ወይም ከቀኑ 10፡00 ሰዓት በኋላ ይሰራሉ፤

**40%** የሚሆኑት በሳምንት ውስጥ ያለ እረፍት በየቀኑ ይሰራሉ፤

**27%** የሚሆኑት በህዝባዊ በዓላት ቀናት ይሰራሉ፤

THE FREEDOM FUND

POPULATION COUNCIL
Ideas. Evidence. Impact.

**የቤት ውስጥ ስራ በኢትዮጵያ ውስጥ በሴቶችና ልጃገረዶች ዘንድ ከተለመዱት የስራ ዓይነቶች አንዱ ነዉ።** ይህ ጥናት የተካሄደበት አካባቢ ከሚኖሩ ከ12 እስከ 17 አድሜ ክልል ከሆኑ ወጣት ሴት ልጆች  የተሰበሰበዉ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ 37 በመቶ የሚሆኑ በቤት ዉስጥ ሰራተኝነት የተሰማሩ ናቸዉ። የወጣት የቤት ዉስጥ ስራ ሁልግዜ ለወጣትዋ ጎጂ ወይም በዝባዥ ነዉ ብሎ መዉሰድ አይቻልም፡ አንዳንድ የቤት ዉስጥ ስራ ለምሳሌ እቤት ዉስጥ ቤተሰብን መርዳት ወይም ከትምህርት ሰዓት ውጪ የኪስ ገንዘብ ለማግኘት መስራት ለወጣቶች አዎንታዊ እና ጤናማ እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ይህ ግን እውን የሚሆነዉ፣ ለተለያዩ ጥቃቶች እና ብዝበዛዎች እንዳይጋለጡ የሕግ ከሌላ ሲኖራቸዉ ነዉ።

**በ2019G.C  የኢትዮጵያ መንግስት በስራ ላይ የተሰማሩ ወጣት ሰራተኞች ላይ የሚደርሰዉን ብዝበዛ ለመከላከል ህጋዊ መስፈርትን የተከተለ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2019 አፀደቀ።** በዚህ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ስር እድሜያቸው ከ15 አመት በታች የሆኑ ልጆች ስራ እንዳይሰሩ ይደነግጋል። ከ15 እስከ 17 አመት የሆኑ ‘ወጣት ሰራተኞች’ በዚህ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት በቀን ከሰባት ሰአት በላይና ፣ ከጠዋቱ 12:00 ሰዓት በፊት ወይም ከቀኑ 10:00 ሰአት በኋላ እና በህዝባዊ በዓላት ላይ እንዳይሰሩ ይከለክላል። እንዲሁም እነኚህ ወጣት ሰራተኞች ቢያንስ በሳምንት አንድ የእረፍት ቀን እንዲኖራቸዉ ይደነግጋል።[1]

**ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሉ ሌሎች ወጣት ሰራተኞች በተመሳሳይ የህግ ማዕቀፍ ከለላ አልተደረገላቸዉም [2]፡** የቤት ውስጥ ስራ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ማዕቀፍ ስር እንዲተዳደር አልተደረገም ፤ እንደ ሌሎች ከለላ የተደረገላቸዉ የስራ ዘርፎች በአዋጁ እዉቅና አልተሰጠዉም። በተጨማሪም የኢትዮጵያ መንግሥት የዓለም አቀፉን የሠራተኛ ድርጅት (ILO, 2011) ‘የቤት ዉስጥ ሠራተኞች ስምምነት ቁጥር 189ን እስካሁን አላጸደቀም። ይህ ስምምነት የቤት ዉስጥ ሠራተኞችን ዝቅተኛ የስራ  ደረጃ ያካትታል።

**በዚህ ሰፊ የዳሰሳ ጥናት ዉጤት መሰረት[3]፣** የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ዉስጥ ከተደነገጉ ድንጋጌዎችን በተጻራሪ **ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ለተለያዩ ብዝበዛዎች የሚያጋልጡ የስራ ሁኔታዎች እንዳሉ ተናግረዋል።** በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ላይ በተደነገገው ድንጋጌ መሰረት እድሚያቸው ከ12-14 ዓመት የሆናቸው ሴት ልጆች በህገ-ወጥ መንገድ እንደሚሰሩ ያመላከተ ሲሆን ከ15-17 ዓመት ከሆናቸው ውስጥ 87 በመቶ የሚሆኑት ሴት ልጆች ህገ-ወጥ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ እንደሚደርስባቸው ይጠቁማሉ። ይህም በመሰረታዊነት ከመጠን በላይ ለረጅም ሰዓት ማሰራት እና ከእረፍት እጦት ጋር በተያያዘ ነው። እነዚህ ወጣት ሰራተኞች በአማካይ በሳምንት ዉስጥ 55 ሰአታት እንደሚሰሩ እና 25 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ በሳምንት ከ70 ሰዓታት በላይ እንደሚሰሩ ተናግረዋል።

**ወጣት የቤት ሰራተኞች በቅድሚያ ልጆች ናቸው!** ከመጠን በላይ ከሆነዉ የሥራ ሰዓታቸዉ ተቀንሶ በቂ የመማር የመጫወቻና የማረፊያ ጊዜ ሊሰጣቸዉ ይገባል። የቤት ዉስጥ ስራ ለሰራተኞችና አሰሪዎቻቸው በኢትዩጵያ የሰራተኛ ሕግ የተደንገገ ጥበቃና ህጋዊነት ያለው የስራ መስክ ሆኖ ሊቀመጥ ይገባል።

የኢትዮጵያን የመንግስት አካላት፤ ፖሊሲ አውጪዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የዚህን ጥናት ምክረ-ሀሳቦችን በማጤን ለወጣት የቤት ሰራተኞች ጥበቃ እንዲያደርጉ ጥሪ እናደርጋለን።

1 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዲሪ) ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፡ “የአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011”፣ ነሐሴ 30፣ 2011፣ አዲስ አበባ

2 ልጅ የቤት ዉስጥ ሠራተኞች” እራሳቸውን እንደ የቤት ሠራተኛነት የገለጹትን እንዲሁም በሳምንት ከ14 ሰዓታት በላይ የቤት ውስጥ ሥራ የሚሰሩ እና ከአባትና ከእናታቸው ጋር አብረው የማይኖሩትን ሴቶችን ያጠቃልላል።

3 ይህ ጥናት በልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ላይ የተሰራ ስሆን፣ ለጥናቱ ናሙና የተወሰዱት 1371 ልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች አድሜያቸዉ ከ12 እስከ 18 የሆኑት ልጃገረዶች ነዉ።

# ምክረ-ሀሳቦችን

- የቤት ውስጥ ስራ ዋና ዋና በሆኑ የሰራተኛ ሕግጋት ውስጥ እንዲካተትና  የአለም አቀፍ የስራ ድርጅት ኮንቬንሽን 189ን ማፀደቅ፡
- የአካባቢ መዋቅሮችን ለምሳሌ እድሮችን፣ የሀይማኖት አባቶችን፣ የቀበሌ እና የወረዳ መዋቅሮችን በመጠቀምና የስምምነት ውል፤ ለሞዴል አሰሪዎች እዉቅና መስጠትና የመሳሰሉትን ስልቶች በመተግበር በወጣት የቤት ሰራተኞች ላይ የሚደርስን ጥቃት መከላከል።
- ወጣት የቤት ሰራተኞች ላይ የሚደርሰዉን መገለል እንዲቆም ምቹ የሆነ ሁኔታን በመፍጠር በራሳቸው የመተማመን ችሎታቸዉ እንዲጨምር፣ ክህሎታቸው እና ማህበራዊ እሴታቸው እንዲያድግ ፤ በስራ ላይ ያሉትን ህጎችና ማእቀፎቻቸው እንዲገነዘቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ከሚገባቸው አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት።
- የሕግ ጥበቃውን በማጠናከር ጥቃት በማድረስ፣ በጉልበት ብዝበዛና የህገወጥ የሰው ዝውውር ለሚጠረጠሩ  የጥቆማ፤ ምርመራና የፍርድ ቤት ሂደቶችን ለልጆች ምቹ ማድረግ።

ይህ ጥናት ከአሜሪካ መንግስት ዲፓርትመንት ኦፍ ስቴትስ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የተዘጋጀ ነው።
እዚህ የተገለጹት አስተያየቶች፣ ግኝቶች እና ድምዳሜዎች የጥናቱ ባለቤቶች እንጂ የአሜሪካ መንግስትን ሃሳብ አያንጸባርቁም።

Read the full report at **https://freedomfund.org/eth-cdw2022/**

**The Freedom Fund (Ethiopia Office)**
Mayswi Building 7th Floor
Ethio-China Ave
Addis Ababa
Ethiopia
+251 (0) 976 - 80 0506

**The Freedom Fund (US)**
315 Flatbush Avenue
#406
Brooklyn, NY 11217
USA
+1 929 224 2448

**The Freedom Fund (UK)**
Lighterman House
30 Wharfdale Road
London, N1 9RY
UK
+44 20 3777 2200

**Population Council**
One Dag Hammarskjold
Plaza
New York, NY 10017
USA
+1 (212) 339-0500

**Population Council**
Heritage Plaza, 4th Floor
Cameroon Street
Addis Ababa,
Ethioia
+251 (0) 116-631712

The Freedom Fund is a United States 501(c)(3) public charity (EIN number 30-0805768).
The Freedom Fund UK is a company limited by guarantee registered in England and Wales (company number 08926428) and a registered UK charity (registration number 1158838).

October 2022

www.freedomfund.org
info@freedomfund.org
@Freedom_Fund